በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ዓለምን አትውደዱ


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ጥቅምት ፲፰ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግቢያ

- “ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።” *1ኛ ዮሐ 2፡15-17፡፡*

-ጌታችን በሁለት አጋጣሚዎች ዓለምን ስለመውደድ አስጠንቅቆናል፡፡ እርሱ ከዚህ ዓለም እንዳልሆነ ሁሉ እኛም ከዚህ ዓለም አለመሆናችንን አስተምሮናል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በዘወትር ቅዳሴዋ ለንፍቁ ዲያቆን የተመረጠው መልእክት ከተነበበ በኋላ ይኸንኑ ታሳስበናለች፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ ዓለም የተፈጠረው ዓለም”፤ የጠፉ ሰዎች፤ በክፉ የሰይጣን ቁጥጥር ሥር የወደቀ ዓለማዊ ጎዳና የተከተለች ዓለም የሚለውንም ትርጉም ከመያዝ ጋር ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡

- **ነገር ግን ክርስቲያኖች ይህን ዓለም እንዳንወድ የተነገረን ለምንድር** *ነው? ዓለም ከሆነው የተነሳ*
- **በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ዓለም**
    - **ቁሳዊው ዓለም አይደለም፤ እግዚአብሔር የፈጠረው መልካም ነውና፡፡**
      “እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን።” *ዘፍጥ 1፡31፡፡*
    - **ሰዎች የምንኖርባትን አይደለም፡፡ ይህንም** “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” ዮሐ 3፡16፡፡
- *ታዲያ መውደድ የሌለብን የትኛውን ዓለም ነው?*
    - **የኃጢአትና የክፋት ዓለም ነው፡፡ ይህም ዓለም ኃጢአት፤ ክፋትና ሰይጣን ተጽእኖ የሚያደርጉበት ዓለም ነው፡፡ ልክ ስፖርት ተጽእኖ የሚያሳድርበት ዓለም የስፖርት ዓለም እንደሚባለው ኃጢአትም ተጽእኖ የሚያደርግበት ወይም ሚዛን የሚደፋበትን ዓለም አትውደዱ አለን፡፡**

# ዓለምን አትውደዱ

- እንደ ኃይለ ቃሉ ይህ የተባለው ዓለም የሚከተሉት ሦስት ነገሮች ውጤት ነው፡፡

1. የሥጋ አምሮት
   - ከሥነምግባር ውጪ የሆነ የሥጋ ግኑኝነት፤ ዝሙት፤ ሕጻናትን/ልጃገረዶችን መድፈር

2. የዓይን አምሮት
   - ይህም የራስ የሆነውን መፈለግ ወይም በቁሳዊ ፍላጎት መገዛት

3. የሕይወት/ኑሮ ትምክህት ወይም ትዕቢት
   - ይህም ከዚህ በፊት በተሠሩ ሥራዎች/በዉጤታማነታችን፤ በገንዘብ፤ ባለንበት ደረጃ፤ ባለን አቅም/ጉልበት… መመካት ነው፡፡ "ትዕቢት ጥፋትን፥ ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።" ምሳሌ 16፡18፡፡

- ዴማስ ለቅዱስ ጳውሎስ ጀርባውን እንዲሰጥ ያደረገው ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ዓለምን መውደዱ ነው፡፡ "ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና፥ ወደ ተሰሎንቄም ሄዶአል፤ ቄርቂስም ወደ ገላትያ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፡፡" 2ኛ ጢሞ 4፡10፡፡

- እነዚህ ሦስቱ ነገሮች በተለያየ ጊዜ በሕይወታችን ላይ ጠንከር ያለ ጥቃት ያደርሳሉ፡፡ እነዚህም፡-
  - ወጣቶች በብዛት በሥጋ አምሮት ይፈተናሉ ይጎዳሉ፡፡
  - በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ (ጎልማሶች) በዓይን አምሮት ይፈተናሉ ይጎዳሉ፡፡
  - ሽማግሎች ደግሞ የሕይወት/ኑሮ ትምክህት ወይም ትዕቢት ይፈተናሉ፡፡

- ከሥነምግባር ውጪ በሆነ ድርጊትም የተነሳ ይሁን በትዕቢት ይህ የተጠቀሰው "ዓለም" ገጽታ ናቸውና ልንወድ አይገባንም፡፡

# ዓለምን አትውደዱ…

***ዓለምን የማንወድበት ሌላኛው ምክንያት አባታችንን እግዚአብሔርን እንዳንወድ የሚያደርገን በመሆኑ ነው፡፡***

- **ኃይለ ቃሉ** ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም በማለት **የሚያስረዳውም ይህንኑ ነው፡፡**

- **ይህን የጻፈው ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ አይደለም፡፡**

- **ቅ. ያዕቆብ** "አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁም ን ? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።" ***ያዕ 4፡4፡፡***

- **ቅ. ማቴዎስ** "ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።" ***ማቴ 6፡24፡፡***

- **እንደ ቅዱስ ዮሐንስ መልእክት የአባት ፍቅር ማለት ትእዛዙን መጠበቅ ማለት ነው፡፡** "ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።" ***1ኛ ዮሐ 5፡3፤ ዮሐ 14፡15፡፡***

# ዓለምን አትውደዱ...

## *ዓለምን ከወደድን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ያቅተናል ወይም አንችልም፡፡*

*ምሳሌ*

- **በዓይን አምሮት ከተሸነፍን የተቸገሩትን እንድንረዳ የሚያዘንን የእግዚአብሔር ሕግ መጠበቅ ይሳነናል፡፡** "ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?" *1ኛ ዮሐ 3፡17፡፡*

- በሕይወት/ኑሮ ትምክህት ወይም ትዕቢት ከተያዝንም ራሳችንን ከሌላው የበለጠ ተፈላጊ አድርገን እናስባለን፤ ጌታችንንም መምሰል ይሳነናል፡፡ "ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።" *ፊል 2፡3-5፡፡*

- **ኃይለ ቃሉ እንደሚነግረን ይህም ዓለም ያልፋል፡፡** "ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፡፡" *1ኛ ጴጥ 1፡24፡፡* "ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፍዋለት ናችሁና። በዚህ ፈንታ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።" *ማቴ 6፡24፡፡*

- **በተቃራኒው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሕጉንም የሚጠብቅ ግን ለዘላለም ይኖራል፤ ሥራቸውም ይከተላቸዋል፡፡** "ከሰማይም። ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ። አዎን፥ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፥ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።" *ራእይ 14፡13፡፡*

# ዓለምን አትውደዱ

- “እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ። በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና።” ***ቆላ 3፡1-24፡፡***

- “እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ።” ***1ኛ ጴጥ 5፡5-6፡፡***

- “ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።” ***ሮሜ 8፡6-8፡፡***
- “ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።” ***ማቴ 6፡24፡፡***
- “ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።” ***ገላ 1፡10፡፡***
- “በራሴ ላይ ምንም አላውቅምና፥ ነገር ግን በዚህ አልጸድቅም፤ እኔን የሚፈርድ ግን ጌታ ነው። ስለዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል። ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አንዱ በአንዱ ላይ አንዳችሁም እንዳይታበዩ። ከተጻፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ፥ ይህን በእናንተ ምክንያት ስለ ራሴና ስለ አጵሎስ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ። አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው? ” ***1ኛ ቆሮ 4፡4-7፡፡***

- “ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን? በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ፥ እነሆ፥ ክፉ ነገርን አመጣለሁና አትፈልገው፥ ይላል እግዚአብሔር ነገር ግን በሄድህበት ስፍራ ሁሉ ነፍስህን እንደ ምርኮ አድርጌ እሰጥሃለሁ።” ***ኤር 45፡5፡፡***

# ማጠቃለያ

- ዓለም በኛ ውስጥ እንዲኖር ሳንፈቅድለት በዚህ ዓለም እንኑር፡፡ ሃገራችን በሰማይ እንደሆነ በማስተዋል ከዚህ ዓለም ኃጢአት "የተዘጋ ምንጭ የታተመም ፈሳሽ" እንሁን፡፡ *መኃልይ 4፡12፤ ፊል 3፡20፡፡*

- ዓለም ምን እንደሆነች በአግባብ ከተረዳን፤ ዓለምን መውደድ ምን እንደሚያደርግ ካወቅን፤ ዓለምም ወዴት እንደምትደርስ ከደረስንበት ለምን "ዓለምን አትውደዱ" እንደተባልን ይገባናል፡፡

- ታዲያ መንገዱ እዚህ ላይ አይቆምም፤ ዓለምን አለመውደድ ለሕይወታችን የተዘጋጀው የታላቁ የእግዚአብሔር ... እግዚአብሔርን የመውደድ እቅድ የመጀመሪያ ደረጃ ነው፡፡

- "የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል። ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል፡፡" *2ኛ ጴጥ 3፡10-11፡፡*

- አትኩሮታችን ልንኖርበት ለምንናፍቀው ለዘላለሙ ሕይወት ወይስ ለዛሬ? ለጡረታችን እንዲሆነን የዚህን ዓለም ሀብት በማከማቸት ላይ ነው ወይስ ለዘላለም ሕይወት በሰማይ?

- ዛሬ የምናስበው ሰዎች ስለኛ የሚያስቡትን ወይስ በፍርድ ቀን ጌታችን ሊያደርገን ስለሚችልበት ቦታ? ዛሬም ዓለምን አንውደድ፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

ይቆየን፡፡